

ነገረ ማርያም

ለ4ተኛ ዓመት የኮርስ ተማሪዎች

በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ማኅበረ ቅዱሳን ትምህርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት ዋና ክፍል የተዘጋጀ

መግቢያ

- በነገረ ድህነት ትምህርት ውስጥ “ምክንያተ ድህነት” የሆነችውን የእመቤታችንን ነገር ማወቅና መረዳት እጅግ አስፈላጊ ነው።

  ምክንያቱም እግዚአብሔር ተወለደ ሰው ሆነ ስንል እንዴት ሰው ሆነ የሚለው ጥያቄ መመለስ ያለበት ስለሆነ ነው።
- ከአዳም መርገም በልዑል እግዚአብሔር ቸርነት ተጠብቃ የቆየች መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል የነገራትን ቃል በፍፁም እምነት ተቀብላ እንደ ቃልህ ይደረግልኝ በማለትዋ እግዚአብሔር ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ፍፁም ሰው በመሆን እናት ትሆነው ዘንድ የመረጣት ሰዎችን ለማዳን ባደረገው ጉዞ ውስጥ ሁሉ መከራን ተቀብላ ያገለገለች ስለሆነ ስለ እመቤታችን መማር ነገረ ድኅነትን ለመረዳት መሰረታዊ ጉዳይ ነው።
- ከዚህም በላይ ምልዕተ ጸጋ ምልዕተ ክብር ስለሆነች ሰዎች ነገረ ድህነትን አምነው በምግባር ለመኖር ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ በሚያደርጉት ተጋድሎ ውስጥ ረዳት ምርኩዝ ልትሆናቸው የተሰጠች ስለሆነ አማላጅነትን ጸጋዋን በረከትዋን እየተማፀኑ መኖር የኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን የነገረ ድኅነት አስተምህሮ አካል ነው።

- ከዚህ አንፃር ይህንን ትምህርት ተማሪዎቹ እመቤታችን ነገረ ድህነት ያላትን ቦታ እንዲገነዘቡ ቅድሳናዋን አማላጅነትዋንና በረከትዋን ትንቢቶችና ምሳሌዎች እዲረዱና በረከትዋን ቃል ኪዳንዋን አምነው የበለጠ እንዲጠቀሙ ከማድረግ አንፃር ይህ መፅሐፍ ተዘጋጅቷል።
- ነገረ ማርያም በሚል ርእስ በአዲስ መልክ የተዘጋጀው ይህ የመማሪያ መፅሐፍ ማኅበረ ቅዱሳን አዲስ በከለሰው ሥርዓተ ትምህርት መሠረት የተሰናዳ ነው። አገልግሎቱ በዋናነት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላሉት የግቢ ጉባኤያት ተማሪዎች ሲሆን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲን እምነት ተከታዮች ለሆኑ ምዕመናን በሙሉ እንዲጠቅም ሆኖ ተዘጋጅቷል።

ረድኤተ እግዚአብሔር አይለየን

አሜን

ምዕራፍ አንድ

- ስለ እመቤታችን ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ወይም ነገረ ማርያም የተሰኘውን ትምህርት ለምን መማር እንዳስፈለገ እና የትምህርቱን የት መጣውን የምንማርበት ነው። በዚህ ክፍለ ትምህርት የነገረ ማርያም መሠረታውያን የሆኑትን ማለትም

- ነገረ ማርያም ማለት ምን ማለት ነው?
- ነገረ ማርያምን መማር ለምን አስፈለገ?
- የነገረ ማርያም ትምህርት ምንጮች ምን ምን ናቸው? የሚሉትን የምናትትበት ነው።

<u>ጥያቄ</u>

ሀ. ነገረ ማርያም ማለት ምን ማለት ነው?አብራራ (ሪ)

ለ. የነገረ ማርያም ትምህርት መማር ጥቅሙ ምንድን ነው?

ነገረ ማርያም ማለት ምን ማለት ነው?

- ከሁለት ቃላት የተገኘ /የተሰናሰለ/ ሲሆን እንደ ቤተ ክርስቲያናችን አስተምህሮ ስለ እመቤታችን ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ንፅህና ፣ ቅድስና ፣ ዘለዓለማዊ ድንግልና ወ.ዘ.ተ የምንማርበት እንዲሁም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በሰው ልጆች መዳን ውስጥ(በነገረ ድህነት) ያላትን ሱታፌ (አስተዋጽኦ) የምንረዳበት የትምህርት ክፍል ነው።

ነገረ ማርያምን መማር ለምን አስፈለገ?

ሀ.ክርስትናን በአግባቡ ለመረዳት፦ ክርስትና አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር በሥጋ ማርያም ተገልጦ የመሠረታት ና ት።

ቅድመ ዓለም ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ትክክል ሆኖ ዓለምን የፈጠረ እና የሚገዛ እግዚአብሔር ቃል (ወልድ) ድህረ ዓለም የጠፋውን አዳምን ፍለጋ በትሕትና እራሱን ዝቅ አድርጎ በሰው ባህርይ መገለጡን ፍፁም አምላክ ፍፁም ሰው መሆኑን የምናምንበት የምንረዳበት ትምህርት ነው።በዚህ በነገረ ድህነት የክርስትና ትምህርት ሰፊውን ድርሻ ይዛ የምትገኘው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናት።

- እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ዓለም ሁሉ ለዳነበት ምስጢር መፈጸሚያ መቅደስ ለመለኮት ማደሪያ እነድትሆን ተመርጣለች።
- በሰዎች ላይ ሰልጥኖ የነበረው የጨለማው ገዢ ዲያብሎስ ድል የተነሳበት አዳም ከጨለማ ግዞት ነፃ የወጣበት አማናዊ ብርሃን ፀሐየ ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስ የተገኘባት ምስራቅ የድህነታችን መሠረት የመዳናችን ምክንያት በመሆኗ ነገረ ማርያምን ትምህርት መማር አስፈልጓል።

ለ.<u>ስለ እመቤታችን ፀጋ እና ክብር ለማወቅ</u>፦ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከአምላካችን ከልዑል እግዚአብሔር በተሰጣት ፀጋ ከነገደ መላእክት ከደቂቀ አዳም በክብር የሚመስላት በፀጋ የሚተካከላት የለም ። ይኸውም ከፍጡራን መካከል ተለይታ የአምላክ እናት ለመሆን የተመረጠች ፣አምላክን በህቱም ድንግልና ፀንሳ በህቱም ድንግልና የወለደች ፣ሁሉን የሚመግበውን አምላክ ጡቶቿን አጥብታ ያሳደገች በጀርባዋ ያዘለች፣ ስለ ልጇ የተሰደደች ፣በመዋለ ማስተማር ዘመኑ ከጌታችን ጋር የነበረች ፣እስከ እግረ መስቀል ያልተለየች፣ በመሆኗ ስለ እርሷ ስለተሰጣትም ፀጋ እና ክብር ለማወቅ አውቆም ለማክበር ነገረ ማርያም ትምህርት መማር ያስፈልጋል።

ሐ.<u>በሕይወታችን ለመጠቀም</u>፦እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከልጇ ከኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጣት የከበረ ቃል ኪዳን አለ ።

ቃልኪዳኑም “ስምሽን የጠራ ዝክርሽን የዘከረ በቃል ኪዳንሽ የታመነውን ከመከራ ሥጋ ከመከራ ነፍስ አድነዋለሁ በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስ እሰጠዋለሁ” የሚል ነው።ይህ ቃል ኪዳን በህይወታችን እንዲሰራ በነፍስም በሥጋም ከኃጢአት በስተቀር የምንፈልገውና የሚገባን (የሚጠቅመን) ነገር እንዲፈፀምልን ይህንን የምናውቅበትን እና የመንረዳበትን ትምህርት ነገረ ማርያምን መማር ያስፈልጋል።

የነገረ ማርያም ትምህርት ምንጮች

- የነገረ ማርያም ትምህርት ልብ ወለድ ፈጠራ ሳይሆን ምንጭ አለው። ምንጩም የመንፈሳውያን መጻሕፍትና ትምህርት መሰሠረታቸው የሆነ መፅሐፍ ቅዱስ ነው።
- ይኸውም በሁለት የተከፈለ ነው “ብሉይ ኪዳን እና ሐዲስ ኪዳን”። በዚሁ በብሉይ ኪዳን እና በሐዲስ ኪዳን የእመቤታችን ነገር በዘመነ ብሉይ በአበው ቀደምት ምሳሌ በነቢያት ትንቢት የተገለጠ፣ በዘመነ ሐዲስ በሐዋርያት ስብከት ፍፃሜውን አግኝቶ የተሰበከ በመሆኑ ቅዱስ መፅሐፍ የነገረ ማርያም ምንጭ ነው።
- ከመፅሐፍ ቅዱስ ቀጥሎ የነቢያትን የሐዋርያትን አስረ ፍኖት ተከትለው ሊቃውንት በድርሰታቸው የእመቤታችንን ነገር ገልጠው ፅፈዋል ።

በተለይ በጊዜው ከተነሱ መናፍቃን ለክህደት ትምህርታቸው መልስ ለመስጠት ባዘጋጁት በሃይማኖተ አበው የነገረ ማርያም ትምህርት የተገለጠ በመሆኑ ለነገረ ማያርም ትምህርት ምንጭ ሆኗል።

- ከዚህ በተጨማሪ ለነገረ ማርያም ትምህርት ምንጭ የሚሆኑ ተአምረ ማርያም፣የቅዱስ ያሬድ የድጓ ድርሰት፣የአባ ጊዮርጊስ ድርሰቶች ማለትም፡-እነ አርጋኖን ዘእግዝእትነ ማርያም፣እነ ሆሕተ ብርሃን፣እነ እንዘራ ስብሐት፣መዓዛ ቅዳሴ የአባ ሕርያቆስ ቅዳሴ የቅዱስ ኤፍሬም ውዳሴ ወ.ዘ.ተ ያሉ ድርሰቶች ናቸው።
- እነዚህን ድርሰቶች ያስደረሳቸው እና የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን ነገር የገለፀላቸው ያደረባቸው እና የመረጣቸው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው። መንፈስ ቅዱስ ያላደረበት የእመቤታችን ክብር ገልፆ መናገር አይችልምና።(ሉቃ 1፥39)።
- በኤልሳቤጥ መንፈስ ቅዱስ መላባት ድምጿን ከፍ አድርጋ የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጪ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል? አንቺ ከሴቶች ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ የማህፀንሽ ፍሬ የተባረከ ነው.....።አለች” እንዲል።

ማጠቃለያ

- የነገረ ማርያም ትምህርት መግቢያ የሚሆን ነገረ ማርያም ማለት ምን ማለት እንደሆነ ነገረ ማርያምን ትምህርት መማር ክርስትናን በአግባቡ ለመደራት ስለ እመቤታችን ፀጋ እና ክብር ለማወቅ እንዲሁም በእመቤታችን ምልጃ በቅድስና ህይወቷ በህይወታችን ለመጠቀም ብሎም የነገረ ማርያም ትምህርት ምንጮች መፅሐፍ ቅዱስና እና ሌሎች አዋልድ መፃህፍት መሆናቸውን ለማሳየት ተሞክሯል። በይበልጥ ደግሞ በነገረ ማርያም ዙሪያ የተፃፉ ነገሮችን ማንበብ ይረዳል።

<u>ዋቢ መፃሕፍት፡-</u>

1. መፅሐፍ ቅዱስ
2. “ወላዲተ አምላክ” በመፅሐፍ ቅዱስ ቀሲስ ደጀኔ ቀሲስ እሸቱ
3. “ነገረ ማርያም” ማኅበረ ቅዱሳን ት.ሐ.አ.